# ❖መልክአ ጉባኤ በግእዝና በአማርኛ ማስታዎሻ❖



አዘጋጅ፡- በትረ ማርያም አበባው ካሣ

(የመጻሕፍት ሊቃውንት፣ የመጻሕፍት ብሉያትና የመጻሕፍት መነኮሳት ትርጓሜ መምህር)

ነሐሴ ፳፪፣ ፳፻፲፫

## ❖መልክአ ጉባኤ በግእዝና በአማርኛ❖

ጉባኤ አስተጋብአ=ሰበሰበ ከሚለው የግእዝ ቃል የወጣ ነው፡፡ ስለዚህ መልክአ ጉባኤ የጌታንና የቅዱሳንን መልክእ ሰብስቦ የያዘ በመሆኑ ይህንን ስያሜ አግኝቷል፡፡

### ✿መልክአ ኤልያስ✿

በመልክእ መክሥተ ግብር [ሥራን ገልጦ መለመን፤ ግብርን መንገር፤ የሆነውን ድርጊት ማሳየት] የተለመደ ነው፡፡ ለምሳሌ መልክአ ኤልያስ ሲጀምር ኦ ኤልያስ ዘወሀብኮ ካዕበተ መንፈስ ምስለ ሐሜለት ለረድዕከ ኤልሳዕ ገባሬ ኀይላት ይላል፡፡ ትርጉሙ ኀይላትን ለሚያደርግ ለተማሪህ ኤልሳዕ እጥፍ መንፈስን የሰጠኸው ኤልያስ ሆይ ማለት ነው፡፡ ሰላም ለትርጓሜ ስምከ ዘተብህለ ዘይተ… [ዘይት ለተባለ የስምህ ትርጉም ሰላም እላለሁ]፡፡ እኩየ ስመ ኢተሀበኒ እንበለ እግበር እኪተ…[ክፉ ሥራን ሳልሠራ ክፉ ስምን አትስጠኝ]፡፡ ሰላም ከርሥከ ላይ አኮኑ ሀገርከ ሀገረ ተድላ ወፍግዕ ከመ ኮነ ስምዐ እስክንድር ስምዕ [ምስክር እስክንድር እንደ መሰከረ ሀገርህ የደስታና የተድላ ሀገር ናትኮ] ይላል፡፡ ለሐቌከ ላይ ደግሞ ጸጓር ሰብእናከ ወንብረትከ ገዳም [ሰውነትህ ጸጉራም አኗኗርህ ገዳም ነው] ይላል፡፡ ለምጽአትከ ላይ ለምጽአተ ክርስቶስ ዘይቀድሞ ሱባኤ ሰንበታት ስሳ ድኅረ ፈጸምከ ፈጽሞ [ስልሳ ሱባኤን መፈጸምን ከፈጸምክ በኋላ የክርስቶስን ምጽአት የሚቀድመው መምጣትህ] ይላል፡፡ ኩነኒ ኖላዌ ኢይምሥጡኒ ለበግዕከ እመርዔትየ ውርዛዌ ተኵላተ ዕድሜ ረኀብ ወጽኑዕ ደዌ ይላል፡፡ ትርጉሙም ከመሰማሪያዬ ጉልምስና የዕድሜ ተኵላዎች የሆኑ ጽኑ ሕመምና ረኀብ እንዳይነጥቁኝ ጠባቂ ሁነኝ ማለት ነው፡፡ መጨረሻ ላይ ኤልያስ ዘኮንከ ሕገ መነኰሳት ሠራዔ ይላል፡፡ ይህም ማለት ኤልያስ ሆይ የመነኮሳትን ሕግ የሠራህ ነህ ማለት ነው፡፡

### ❁መልክአ ዮሐንስ መጥምቅ❁

ለሥዕርተ ርእስከ ላይ ርእሰ ዐውደ ዓመት ዮሐንስ ወላዴ መጥቅዕ ወአበቅቴ ይላል፡፡ ትርጉሙም አበቅቴና መጥቅዕን የምታስገኝ ዮሐንስ የዐውደ ዓመት ራስ [መጀመሪያ] ነህ ማለት ነው፡፡ ለእራኅከ ላይ ዮሐንስ ጸሊ ኀበ ሊቅከ ኢያሱ ይላል፡፡ ትርጉሙም ዮሐንስ ሆይ ወደ መምህርህ ኢየሱስ ጸልይ ማለት ነው፡፡ ለአማዑቲከ ላይ ሰላም ለአማዑቲከ እግዚአብሔር ዘገብሮ ይላል፡፡ ትርጉሙ እግዚአብሔር ለፈጠረው አንጀትህ ሰላም እላለሁ ማለት ነው፡፡ ለሰኳንዊከ ላይ ዮሐንስ ነፋስ ለጸበለ ጌጋይ ዘትዘርዎ ይላል፡፡ ትርጉሙ በደል ትቢያን [አቧራን] የምትበትነው ነፋስ ዮሐንስ ነህ ማለት ነው፡፡ ለፀአተ ነፍስከ ላይ ዮሐንስ ፍትው ወጽዕድው እምወራውሬ ይላል፡፡ ትርጉሙ ዮሐንስ ሆይ ወራውሬ ከሚባል ዕንቊ ይልቅ የምትነጻና የምትወደድ ነህ ማለት ነው፡፡

## ✿መልክአ ሊባኖስ✿

ሕያው በሆነና የማይሞት አምላክ በሆነ በእግዚአብሔር ስም እንዲሁም ሑከትንና መርገምን በሻረች በድንግል ማርያም ስም የመልክእህን ምስጋና እያከታተልኩ በመጨመር እጆፍ ዘንድ አባት ሆይ በተባረከ መስቀልህ ባርከኝ፡፡ (#በግእዝ፦ በስመ እግዚአብሔር ሕያው ዘኢይመውት አምላክ ወበስመ ማርያም ድንግል ሰዓሪተ መርገም ወሀውክ ውዳሴ መልክእከ እጽሐፍ እንዘ አተሉ በተውሳክ ባርከኒ አባ በመስቀልከ ቡሩክ)፡፡ ለአፅናፊከ ላይ ሊባኖስ ዮሐንስ ረአዩ ኀቡዓት ዘምድረ ፍጥሞ ይላል፡፡ ትርጉሙ ሊባኖስ ሆይ በምድረ ፍጥሞ ምሥጢርን ያየህ ዮሐንስ ነህ፡፡

## ❁መልክአ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ❁

የምሥራች ሐዋርያና የአዲስ ዜና ተናጋሪ የሆንክ ዮሐንስ ሆይ የክብርህን ነገር አይ ዘንድ የሁሉ ገዢ የሆነ ኅሊና አዘዘኝ፡፡ ሐዋርያ ብሥራት ዮሐንስ ወፀዋሬ ሐዲስ ዜና ነገረ ስብሐቲከ እርአይ አዘዘኒ መኰንነ ኵሉ ኅሊና፡፡ ለከናፍሪከ ላይ ለከናፍሪከ ጽሩዓት እምተግባረ ነቢብ ምድራዊ ምስለ ደኃራይ ሥጋ ተዋሕዶተ ቃል ቀዳማዊ በመንፈስ ቅዱስ ዮሐንስ ለባዊ ይላል፡፡ ትርጉሙ ዮሐንስ ሆይ ምድራዊ ከሆነ ነገር ለተከለከሉ ከንፈሮችህ ሰላም እላለሁ፡፡ ደኃራዊ የሆነ ሥጋንና ቀዳማይ የሆነ ቃልን መዋሐድ በመንፈስ ቅዱስ የተረዳህ ነህ ማለት ነው፡፡ ለጕርጔከ ላይ ዳዊት ዮሐንስ ጎልያድሀ ሰይጣነ ቀተልከ ነሚአከ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ዕብነ ይላል፡፡ ትርጉሙ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ድንጋይን ይዘህ ሰይጣን ጎልያድን የገደልክ ዮሐንስ ዳዊት አንተ ነህ ማለት ነው፡፡ ለሕፅንከ ላይ በስንከ መንፈሳዊ እምእለ ሳውል ወኬፋ አፍቀረከ ጥቀ ፍቁርከ አልፋ ይላለ፡፡ ትርጉሙ መንፈሳዊ በሆነ ውበትህ ከእነ ሳውልና ከነ ኬፋ ይልቅ ወዳጅህ አልፋ በጣም ወደደህ ማለት ነው፡፡ በተድላ አልጋ ላልተኛ ጎንህ ሰላም እላለሁ፡፡ በእግዚአብሔር ፍቅር ለተራብ ሆድህም ሰላም እላለሁ፡፡ ሰላም ለገቦከ በአራተ ተድላ ዘኢሰከበ ወለከርሥከ በፍቅሩ ለእግዚአብሔር ዘርኀበ፡፡ ለሐቌከ ላይ ሶበ ደምፀ ወተሰምአ ድምፀ ቃልከ ሕይወት ጉባኤ አጋንንት ተዘርወ ወተነጽሐ ሞት ይላል፡፡ ትርጉሙ የሕይወት ቃልህ ድምፅ ፈጽሞ በተሰማ ጊዜ የአጋንንት ጉባኤ ተበተነ ሞት ተጣለ፡፡ ለአእጋሪከ ላይ ነሣኤ ክህነተ ዮሐንስ እምሊቀ ካህናት ዘራማ ሥርየተ ኃጢአት ትስእል ወትበኪ ድኅረ ፍቅርከ ቀዊማ ማርያም ነፍስየ እንተ ይእቲ ዘማ ይላል፡፡ ትርጉሙ ከራማው የካህናት አለቃ ክህነትን የተቀበልክ ዮሐንስ ሆይ ዘማ የሆነች ማርያም ነፍሴ ከፍቅርህ በኋላ ቆማ እያለቀሰች የኃጢአት ሥርየትን ትለምናለች፡፡ ለመከየድከ ላይ ነባቤ መለኮት ዮሐንስ በውስተ ደኃራይ ወንጌል ቃልከ አማናዊ ይጸርሕ ወይብል ሥጋ ሰብእ ኮነ ቀዳማይ ቃል ይላል፡፡ ትርጉሙ የመለኮትን ነገር የሚናገር ዮሐንስ የኋላ በሆነ ወንጌል እውነተኛ በሆነ ቃልህ የሰው ሥጋ ቀዳማዊ ቃልን ሆነ እያለ አሰምቶ ይናገራል፡፡

## ❧መልክአ ገብረ መንፈስ ቅዱስ❧

ገብረ መንፈስ ቅዱስ ጳውሎስ በጉባኤ ውስጥ ሃይማኖትን የሚሰብክ ነው፡፡ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ጳውሎስ ሰባኬ ሃይማኖት ውስተ ኵርጓኔ፡፡ ለእመታቲከ ላይ ሙተተ ነፍስየ አሕዩ ገብረ

መንፈስ ቅዱስ ሕያው ወቀስም ልስሐትየ ለሐዋርያት አበው ከመ ቀሰሞሙ ጳራቅሊጦስ ጼው ይላል። ትርጉሙ ሕያው የሆንክ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሆይ የሰውነቴን መሞት አድን። ጨው ጳራቅሊጦስ አባቶች ሐዋርያትን እንዳጣፈጣቸው አልጫነቴን አጣፍጥ።

### 🎖መልክአ ጴጥሮስ ወጳውሎስ🎖

ለቀራንብቲክሙ ላይ ወይነ ሃይማኖት ጴጥሮስ ወጳውሎስ ጵርስፎራ ይላል። ትርጉሙ ጴጥሮ የሃይማኖት ወይን ሲሆን ጳውሎስ ደግሞ ዳቦ ነው።

### 🌹ሰቆቃወ ድንግል🌹

**ነገረ ማርያም፦** ጻድቅ ልጅን ስለወለድሽ ከጥንት ጀምሮ አይሁድ በጣም ይጠሉሻል። የመሐል ራሴ አክሊል ማርያም ሆይ የሱፍ አበባ ነሽ። ለሆድሽ ፍሬ ትሕትና ልማዱ ነውና ባሕርይሽ በቃልም በተግባርም እንደ እርሱ ነው። (#በግእዝ፦ እምትካት አይሁድ በቅንዐቶሙ ይጸልዑኪ ጥቀ በእንተ ዘወለድኪ በድንግልና ወልደ ጻድቀ። ማርያም ጽጌ ደንጎላ ዘድማኅየ ቀጸላ። እስመ ልማዱ ትሕትና ለፍሬ ከርሥኪ ልዑል ከማሁ ግዕዝኪ በምግባር ወቃል)።

**ነገረ ክርስቶስ፦** የስደተኞች ተስፋ የተሰደደ ኢየሱስ ነው። ለተገፉት መጠጊያ ኢየሱስ የተገፋ ነው። (#በግእዝ፦ ኢየሱስ ስዱድ ተስፋሆሙ ለስዱዳን። ኢየሱስ ግፉዕ ምስካየ ግፉዓን)።

### 🌷መልክአ ሥላሴ🌷

**ምሥጢረ ሥላሴ፦** ከአንድነት ልዩ ለሆነና አምላክ በመባል በሚመስለው ከመለየት አንድ ለሆነ ስማችሁ ሰላም እላለሁ። በውጭ ሳላችሁ በውስጥም አላችሁ። ዓለም የሌላችሁ የዓለሞች ዓለም ሥላሴ ሆይ ለእናንተ ቁመት ሰላም እላለሁ። ሥላሴ ሆይ ሦስትነታችሁ ቦታ ያድርገኝ። የሥላሴን ብርሃን ከተዋሐድኩ በኋላስ ሁለንተናዬ ከዚህ ዮርዳኖሳችሁ ሆኗልና የታመነ የሆነ ምስክርነታችሁን ከዮርዳኖስ አልፈልግም እኔ ታቦር ነኝና ታቦርንም አልመኘውም። (#በግእዝ፦ ሰላም ለስምክሙ ዘኢይትጋባዕ እምተከፍሎ ወዘእምተከፍሎ ይትጋባዕ በተሰምዮ አምላክ ዘይመስሎ። ለሕፅንክሙ |እንዘ በአፍኣሁ አንትሙ ወአንትሙ በውሳጤሁ|። ሰላም እብል ለዘዚኣክሙ ቆም ዓለማተ ዓለም ሥላሴ ዘአልብክሙ ዓለም። ሥላሴክሙ ሥላሴ ይረስየኒ መካነ። ድኅረ ተዋሐድኩሰ ዘሥላሴሁ ብርሃነ። ዮርዳኖስክሙ ዝየ እስመ ኮለንታየ ኮነ። ኢየኀሥሥ እምዮርዳኖስ ሰማዕተክሙ ምእመነ ወኢይትሜነዮ ለታቦር እስመ ታቦር አነ)።

**ነገረ ማርያም፦** በድንግል ማርያም የአባቶች ተስፋ ተፈጸመ በቀራንዮም የሚያድን መስቀል ተተከለ። (#በግእዝ፦ ተፈጸመ ተስፋ አበው በማርያም ድንግል ወበቀራንዮ ተተክለ መድኀኒት መስቀል)።

## መልክአ ፬ቱ እንስሳ

**የእግዚአብሔር የሰማዩ ተሸካሚ የሆናችሁ አራቱ እንስሳ ሆይ በዘመናት ከሚለዩ ከአራቱ ከዋክብት ይልቅ ታላቅነቱ ከፍ ላለ የስማችሁ መታሰቢያ ሰላም እላለሁ::** (#በግእዝ፦ ሰላም ለዝክረ ስምክሙ ዘተለዐለ ዕበዩ እምዝክረ ከዋክብት አርባዕ በመዋዕለ አዝማን እለ ይትሌለዩ:: አርባዕቱ እንስሳ ለእግዚአብሔር ፀወርተ ሰማዩ)::

## አርኬ

**ነገረ ማርያም፦** ሰማይን ተመስለሽ ፀሐይን ያወጣሽ፣ እርሻን ተመስለሽ ስንዴን ያፈራሽ ማርያም ሆይ ለኃጥኣን ነፍስ መሸሻ የሆንሽ ነሽ:: (#በግእዝ፦ ተመሲለኪ ሰማየ እንተ አሥረቂ ፀሐየ፣ ተመሲለኪ ገራህተ እንተ ፈረይኪ ሥርናየ፣ ማርያም ዘኮንኪ ለነፍሰ ኃጥኣን ምጕያየ)::

**ነገረ ክርስቶስ፦** ክርስቶስን አስቡት መልካም ነገሩንም አትርሱ:: (#በግእዝ፦ ተዘከርዎ ለክርስቶስ ወሠናያቲሁ ኢትርሥዑ)::

## መልክአ ውዳሴ

**ነገረ ማርያም፦** ማርያም ድንግል ናት:: ማርያም የኤፍራታ ርግብ ናት:: ድንግል ማርያም የሽቱ ሙዳይ ናት:: ማርያም ፍሬን የተሸከምሽ አበባ ነሽ:: ያማረ የሰማይ ኮከብን እና ፀሐይን ትወልጂ ዘንድ የተገባሽ የተባልሽ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ:: (#በግእዝ፦ ማርያም ድንግል ማርያም ርግበ ኤፍራታ:: ማርያም ድንግል ሙዳየ አፈው:: ማርያም ጽጌ ዘትጸውሪ አስካለ:: ተፈሥሒ ማርያም ዘተሰመይኪ ድልወ ከመ ትለዲ ፀሐየ ወኮከበ ሰማይ ሥርግወ)::

**ነገረ ክርስቶስ፦** ኢየሱስ ክርስቶስ በአንቺ ላይ ባደረ ጊዜ ንጹሕ ሥጋሽን ከመለኮቱ ጋር አዋሐደ:: (#በግእዝ፦ ኢየሱስ ክርስቶስ አመ ላዕሌኪ ኀደረ ሥጋኪ ንጹሐ ምስለ መለኮቱ ደመረ)::

## መልክአ መስቀል

**ነገረ ክርስቶስ፦** ክርስቶስ የፍቅር መሰላል ነው:: ከገዢው ጲላጦስ ወታደሮች ዘንድ ምራቅን ለታገሠ ፊትህና በእሾህ አክሊል ላጌጠ ራስህ ሰላም እላለሁ:: ክርስቶስ የሃይማኖት አለት ነው:: የፍቅር ቁልፍ ክርስቶስ እንደ ኔስታሊ የተሰቀለ ነው:: ዝናምን የምትሰጥ አንተን ውሃን ከለከሉህ:: የካህናት አለቃ ክርስቶስ ሆይ ከመሠዊያ ሁሉ በላይ ነህ:: ከዓለም ገንዘብ የተራቆትክ ክርስቶስ ሆይ የአብ ልብስ ነህ:: ክርስቶስ የትንሣኤ በኵር ነው:: ስሙ የሚጣፍጥ ክርስቶስ የቃለ ዐዋዲ ዮሐንስ ሞገስ ነው:: (#በግእዝ፦ ሰዋስወ ፍቅር ክርስቶስ:: ሰላም ለርእስከ ሥርግወ አክሊል ዘሦክ ወዕገሠ ምራቅ ገጽከ እምሐራ ጲላጦስ መልአክ:: መራኍተ ፍቅር ክርስቶስ ስቁል ከመ ኔስታሊ:: ኰኵሐ ሃይማኖት ክርስቶስ:: ለወሃቤ ዝናም ክርስቶስ ዘከልዑከ ማየ:: ልብሰ አብ ክርስቶስ እምንዋየ ዓለም ዕሩቅ:: ሊቀ ካህናት ክርስቶስ ዘመልዕልተ ኵሉ ምሥዋዕ:: በኵረ ትንሣኤ ክርስቶስ:: ጥዑመ ስም ክርስቶስ ሞገሰ ዮሐንስ ቃለ ዐዋዲ)::

### 🍍መልክአ ሐና🍍

**ሐና፦** ሐና ሆይ የአሮን በትር አበባና የሙሴ የወይን ሐረግ ነሽ። ሐና በምድርና በሰማያት ከከበሩት የከበረች ናት። ሐና የዕለታት መጀመሪያ የተባለች እሑድ ናት። (#በግእዝ፦ ጽጌ በትረ አሮን ሐና ወዘወይነ ሙሴ ሐረግ። ብፅዕተ ብፁዓን ሐና በምድር ወበሰማያት። ርእሰ ዕለታት ሐና እንተ ይእቲ እሑድ)።

### ●መልክአ ያሬድ●

ያሬድ ሆይ በአክሱም መቅደስ አንቀጸ ብርሃንን መናገር በጀመርክ ጊዜ በጸጋ ውሃ የታጠበ ተረከዝህ ከምድር አንድ ስንዝር ያህል ከፍ ብሎ ተገኘ። (#በግእዝ፦ አንቀጸ ብርሃን ያሬድ አመ ወጠንከ ነቢበ። በመቅደሰ አክሱም ሰኰናከ ዘበማየ ጸጋ ተሐፅበ። መጠነ እመት እምነ ምድር ልዑለ ተረክበ)።

### 🍎መልክአ ሳሙኤል🍎

ሳሙኤል በቅድስናና በንጽሕና ያጌጥክ ነህ። ስለ ድካምህና ብዙ ስለሆነ ትዕግሥትህ ፊንታ የሚያስፈራ አንበሳ ተገዛልህ። (#በግእዝ፦ ሳሙኤል ሥርግው በቅድስና ወንጽሕ ህየንተ ፃማከ ወትዕግሥትከ ብዙኅ ገረረ ለከ አንበሳ መፍርህ)።

### 🍒ነግሥ🍒

**እግዚአብሔር፦** በአንዲት ቃል ዓለምን ሁሉ ለፈጠረ ፈጽሞ የተመሰገነ፣ ታላቅ የሆነና ያለ እግዚአብሔርን እናመስግነው። ለአብ ሰላም ለቃሉ ወልድም ሰላም አካላቸው አካሉ ለሆነ መንፈስ ቅዱስም ሰላም። የማርያምን ሥጋ ለለበሰ ለወልድም ሰላም። (#በግእዝ፦ ንወድሶ ለዘሀሎ እግዚአብሔር ልዑል ስቡሕ ወውዱስ ዘሣረረ ኵሎ ዓለመ በአሐቲ ቃል። ሰላም ለአብ ወለወልድ ቃሉ ወለመንፈስ ቅዱስ ሰላም ዘአካሎሙ አካሉ። ለወልድ ሰላም ሥጋ ማርያም ለባሲ)።

**ነገረ ማርያም፦** እንደ ልጅሽ ደም ጣዕሙ ድንቅ ለሆነ ለስምሽ መታሰቢያ ሰላም እላለሁ። ማርያም ሆይ የሕይወት መሠረት፣ ዓለሙን ለመቤዠት ከሁሉ አስቀድሞ አንቺን መልካሚን የፈጠረ የመድኃኒት መጀመሪያ ነሽ። (#በግእዝ፦ ሰላም ለዝክረ ስምኪ ዘመንክር ጣዕሙ ለወልድኪ አምሳለ ደሙ መሠረተ ሕይወት ማርያም ወጥንተ መድኀኒት ዘእምቀዲሙ ኪያኪ ሠናይተ ዘፈጠረ ለቤዛ ዓለሙ)።

### 🌶መልክአ ሚካኤል🌶

ከልዑል ስም ጋር አንድ ለሆነ ስምህ መታሰቢያ ሰላም እላለሁ። ከውሃና ከመሬት ላልተቀላቀለ ከነፋስና ከእሳት ለተሣለ ፊትህ ሰላም እላለሁ። የራማ ንጉሥ የምስጋናን ቃል ለማያስታጉሉና ዝም ለማይሉ ከንፈሮችህ ሰላምታ ይገባል። ስለ ሙሴ ሥጋ ከሰይጣን ጋር በተባባለ ጊዜ

ስድብን በመናገር ሳልተደፋፈረ አንደበትህ ሰላም እላለሁ። ሰው ነገ የምትወልደውን አያውቅም። (#በግእዝ፦ ሰላም ለዝክረ ስምከ ምስለ ስመ ልዑል ዘተሳተፈ። ሰላም ለገጽከ እምነፋስ ወነድ ዘተሥዕለ ምስለ ማይ ወመሬት ዘኢተሐወለ። ሰላም ለከናፍሪከ እለ ኢያጸርኣ ወኢያረማ ቃለ ቅዳሴሁ ለንጉሠ ራማ። ሰላም ለልሳንከ በነቢበ ጽርፈት ዘኢተሐበለ በእንተ ሥጋሁ ለሙሴ አመ ምስለ ሰይጣን ተበሀለ። እስመ ኢየአምር ሰብእ ዘትወልድ ሳኒታ)።

## ❦መልክአ ሩፋኤል❦

ሩፋኤል ባለ መድኀኒት ነው። አንድ የሆነ ሩፋኤል የአእላፍ አለቃ ነው። ለሁሉ ምሕረትን የምትለምን ሩፋኤል ሆይ ለሰውና ለእንስሳ ፈታሔ ማሕፀን አንተ ነህ። (#በግእዝ፦ ሩፋኤል ዐቃቤ ሥራይ። ሩፋኤል አሐዱ ሊቀ አእላፍ። ሩፋኤል ለኵሉ እንተ ትስእል ምሕረተ ለሰብእ ወለእንስሳ ፈታሔ ማሕፀኖሙ አንተ)።

## ✤መልክአ አእላፍ✤

ትጉሃን አእላፍ ለማመስገን የምትተጉ ናችሁ። በሚች ሰው መታመን ከንቱ ነው። (#በግእዝ፦ ትጉሃን አእላፍ እለ ትጽሕቁ ለዘምሮ። ተአምኖተ ሰብእ መዋቲ አምጣነ ከንቱ ውእቱ)።

## ⸸መልክአ አረጋዊ⸸

የዋህ አረጋዊ የማይቀየም ዳዊትን የሚመስል ነው። በክርስቶስ የፍቅሩ ገመድ የተያዝክ አረጋዊ ሆይ በየጠዋቱ ከክርክር ነገር አርቀኝ። ከእርሱ ትካዝ ይወለዳልና። (#በግእዝ፦ አረጋዊ የዋህ ተመሳሌ ዳዊት ኢተቀያሚ። አረጋዊ ለክርስቶስ በሐብለ ፍቅሩ እንትዝ አግሕሰኒ ለለጽባሑ እምነገረ ተስናን ወጋዕዝ እስመ እምኔሁ ፍጹመ ይትወለድ ትካዝ)።

## ✿መልክአ ቁርቆስ✿

የፊትህ ክበብ ደምን እስኪታለል ድረስ ከቆዳው ጋር ለተላጨ ራስህ ሰላም እላለሁ። ድንቅን የምታደርግ ቁርቆስ ሆይ ምልክአም እንደተባለ እንደ ሙሴ ኃጢአቴን ፈርዖንን ወደሚያሰጥም የምሕረት ባሕር ወርውረህ ዛሬ አስጥመው። (#በግእዝ፦ ሰላም ለርእስከ ምስለ አነዳሁ ዘተላጸየ ክበበ ገጽከ ደመ እስከ ተሴረየ። ገባሬ መንክራት ቁርቆስ በአምሳለ ሙሴ ምልክአም፣ ለፈርዖን ኃጢአትየ ውስተ ባሕረ ምሕረት መስጥም፣ ውርዎ እግዚእየ ወአስጥሞ ዮም)።

## ❃መልክአ ኪዳነ ምሕረት❃

**ነገረ ማርያም፦** ከአንቺ በቀር ማዳን የሚቻለው የለምና በኪዳንሽ አድኝኚ ከጥፋትም አድኚኝ። ከመላእክትና ከሰው ይልቅ የተመረጥሽ ማርያም ሆይ ኃጥእ ሰው ጽኑዕ በሆነ መታመን መታሰቢያሽን ቢያደርግ ከአንቺ ጋር በመንግሥተ ሰማያት ይነግሣል። (#በግእዝ፦ አድኅንኒ በኪዳንኪ ወባልሕኒ እምሀጉል እስመ ዘእንበሌኪ አልቦ አድኅኖ ዘይክል። ማርያም ኅሪት እምነ

መላእክት ወሰብእ ተዝካረኪ ለእመ ገብረ በተአምኖ ጽኑዕ በመንግሥተ ሰማይ ምስሌኪ ይነግሥ ኃጥእ)።

## ✝መልክአ ዐቢየ እግዚእ✝

መጀመሪያውና መጨረሻው የፊደል መጀመሪያ አሌፍ ለሆነ ስምህ ሰላም እላለሁ። ከከበሩ የነገሥታት መዓዛ ይልቅ በክርስቶስ መዓዛ በአንድነት ለተመሰጡ አፍንጫዎችህ ሰላምታ ይገባል። ሁልጊዜ ክቡር የሆነውን የፈጣሪን ምስጋና ለሚያነቡ መንፈሳውያን ከንፈሮች ለሆኑ ከንፈሮችህ ሰላምታ አቀርባለሁ። (#በግእዝ፦ ሰላም ለዝክረ ስምከ ዘፊደለ አሌፍ ጥንቱ ወዘፍጻሜሁ በዝንቱ። ሰላም ለአዕናፊከ እለ ተመስጣ ኀቡረ ኀበ መዓዛሁ ለክርስቶስ እመዓዛ ነገሥት ዘከብረ። ሰላም ለከናፍሪከ መንፈሳውያን ከናፍር እለ ያነብባ ወትረ ስብሐተ ፈጣሪ ክቡር)።

## ❤መልክአ ገብርኤል❤

የልደት ሐዋርያ ገብርኤል ሆይ በላይህ ላይ የሕፃንና የእናቱ መልክ የተሳለበት እንዲሁም ማኅተሙ የአይሁድ ንጉሥ የሚል ያለበት የበለዓም የሕልሙ ኮከብ አንተ ነህ። ጌታና አገልጋይ ማለት ይመስላል እንጂ የማይተረጎም ምስጢር ለሆነው ለስምህ መታሰቢያ ሰላምታ ይገባል። ገብርኤል በጠዋት የምትወጣ ፀሐይ ነህ። በዓለም ጠዋት የተናገረውን ማታ የሚደግም ጓደኛ አይገኝም። መሬታዊ የሆነ ሰውስ በከንቱ ይሞታል ሕይወቱም እንደጢስ ያልፋል። (#በግእዝ፦ ሐዋርያ ልደት ገብርኤል ለበለዓም ኮከበ ሕልሙ ዘተሥዕለ በላዕሌከ መልክአ ሕፃን ወእሙ ንጉሠ አይሁድ ዝንቱ ዘይቤ ማሕተሙ። ሰላም ለዝክረ ስምከ ዘኢይተረጎም ምስጢር ባሕቱ ይመስል ብሂለ እግዚእ ወገብር። ገብርኤል ፀሐይ አንተ ትሠርቅ ጽባሐ። በዓለምሰ ኢይትረከብ አርክ በጽባሕ ዘተናገረ ዘይደግም በሠርክ። ሰብእሰ መሬታዊ ይመውት በከንቱ ወአምሳለ ጢስ የኀልፍ ሕይወቱ)።

## 💟ተፈሥሒ ማርያም💟

**ነገረ ማርያም፦** የአዳም ፋሲካውና የኅኑ አጥንት ለሆነችው ለሔዋን መሻገሪያዋ የሆንሽ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ። የልጅሽ ትንሣኤ ነጻነታቸው ሆኗልና። የጠላቱን መውደቅ የሚያይ ሰው ንዑድ ክቡር ነው። ጰንጠቆስጤ የተባልሽ ማርያም ሆይ አንቺ የዕረፍት ጊዜ ነሽ። በሥጋና በኅሊና ድንግል የሆንሽ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ። አንቺ በሲና ተራራ የታየሽ ጳጦስ ነሽ። ቁልፏ ያልተከፈተ በር ሆይ ደስ ይበልሽ። ታቦትና ጽላት የሆንሽ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ። የሸቱ ዕቃ የሆንሽ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ። የአዳምና የሔዋን መድኃኒት ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ። አዲስ ጥጃ የተባልሽ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ። (#በግእዝ፦ ተፈሥሒ ማርያም ለአዳም ፋሲካሁ ወማዕዶታ ለሔዋን እንተ ይእቲ ዐፅመ ገቦሁ። እስመ ግዕዛኖሙ ኮነ ለወልድኪ በትንሣኤሁ። ብፁዕ ብእሲ ድቀተ ፀሩ ዘይሬኢ። መዋዕለ ዕረፍት አንቲ ማርያም ጰንጠቆስጤ። ተፈሥሒ ማርያም ድንግልተ ሥጋ ወኅሊና። ጳጦስ አንቲ ዘአስተርአይኪ በደብረ ሲና።

ተፈሥሒ አንቀጽ ዘኢተርሕወ መንስጋ:: ተፈሥሒ ማርያም ታቦተ ሕርመት ወጽሌ ተፈሥሒ ጽሪት ዘዕፍረትየ ቢረሌ:: ተፈሥሒ ማርያም መድኀኒተ አዳም ወሔዋ ተፈሥሒ ማርያም ሐዳስዩ ጣዕዋ)::

**ቅዱስ ጊዮርጊስ፦** በመታመን ለሚጠራህ ከነፋስና ከዐውሎ ይልቅ ለረድኤት የምትፈጥን ጊዮርጊስ ሆይ ለምሕረትና ለይቅርታ ቅርብ ነህ:: ሁልጊዜም ጸሎቴንና የጩኸት ቃሌን ሁሉ ተቀበል:: ልቡ ርኅሩኅ የሆነ አምላክ ከአንተ ዘንድ አለና:: (#በግእዝ፦ ኦ ፍጡነ ረድኤት እምሩፀተ ነፋስ ወአውሎ ለዘይጼውአከ በተወክሎ ጊዮርጊስ ቅሩብ ለምሕረት ወለተሣህሎ ተወከፍ ወትረ ጸሎትየ ወቃለ ጽራሕየ ኵሎ እስመ ርኅሩኅ ልብ አምላክ በኀቤከ ሀሎ)::

## ❤መልክአ ሥዕል❤

**ነገረ ማርያም፦** የመስቀል አጥር የሚከባት ማርያም ምሕረትን የምትለምን ናት:: ለፍጥረት ሁሉ የምትለምን ምሕረት ልማዷ የሆነች ርኅርኅተ ኅሊና ናት:: የተባረከች የሆነች የማርያምን ሥዕል እንሳለማት:: ድንግል ሆይ በየዘመኑ ማሪኝ ይቅር በይኝ:: እመቤቴ ሆይ አንቺ ይቅር ካልሽኝ ማን ይኰንነኛል? የሥጋና የነፍስ ገዢ ልጅሽ አይደለምን?! የፍቅርሽ ጣዕም የሚያስደስት የበርተሎሜዎስ ወይን ማርያም አንቺ ነሽ:: (#በግእዝ፦ ሰአሊተ ምሕረት ይእቲ ማርያም ሐፁረ መስቀል ዘየዐውዳ:: ኦ ርኅርኅተ ኅሊና ዘሕገ ልማዳ ምሕረት ለኵሉ ፍጥረት:: ንሳለማ ንዑ ለሥዕለ ማርያም ቡርክት:: መሐርኒ ድንግል ወተሣሀልኒ በበዘመኑ ለእመ መሐርክኒ እግዝእትየ ዘይኴንነኒ መኑ ኰናኔ ሥጋ ወነፍስ ወልድኪ አኮኑ:: ወይነ በርተሎሜዎስ አንተ ማርያም ዘያስተፌሥሕ ጣዕመ ፍቅርኪ)::

## 💝መልክአ ማርያም💝

ጌታ እግዚአብሔር ገብርኤልን በመሰለ ጊዜ ቃሉን ለሰሙ ጆሮዎችሽ ሰላምታ ይገባል:: የሸማግሌዎች ፈጣሪ ሆኖ ሳለ ሕፃን በሆነ ጊዜ እሳትን ለሳመ አፍሽ ሰላምታ ይገባል:: ነፍስን የሚቀድስና ሙቀቱ የሚያድን የመለኮት መቀመጫ ለሆነ ለደረትሽ ሰላምታ ይገባል:: ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ ከበቀል ሩቅ ለሆነ ልብሽ ሰላምታ ይገባል:: መልካምን ማሰብና ምሕረትን ማድረግ ልማዱ ለሆነ ኅሊናሽ ሰላምታ አቀርባለሁ:: ድንግል ማርያም የካህን የመመረጡ ዕፅ ናት:: ድንግል ማርያም የኪዳን ምልክት የሆነች ቀስተ ደመና ናት:: ድንግል ማርያም የወይን አፀዴ ናት:: ድንግል ማርያም የመንግሥት ሀገር ርግብ ናት:: (#በግእዝ፦ ሰላም ለአዕዛንኪ እለ ሰምዓ ቃሎ እግዚአብሔር እግዚእ ሶበ ለገብርኤል ተመሰሎ:: ሰላም ለአፉኪ ዘሰአመ ርስነ እንዘ አበ አዕሩግ ውእቱ በጊዜ ኮነ ሕፃነ:: ሰላም ለእንግድዓኪ ለእሳተ መለኮት ምርፋቁ ዘይቄድስ ነፍሰ ወያጥኢ ሞቁ:: ሰላም ለልብኪ እምነ በቀል ርትቅ አምጣነ አረብ ወሠርቅ:: ሰላም ለኅሊናኪ ኀልዮ ሠናያት ልማዱ ወገቢረ ምሕረት መፍቅዱ:: ማርያም ድንግል ለካህን ዕፀ ኅርየቱ:: ማርያም ድንግል ትእምርተ ኪዳን ቀስተ ደመና:: ማርያም ድንግል አፀደ ወይንየ:: ማርያም ድንግል ለሀገረ መንግሥት ርግባ)::

## መልክአ ፍልሰታ

**ነገረ ማርያም፦** በእርሷ የያፌዝ ወርቅን ጠቢባን ያስገቡለት የሰሎሞን የተርሴስ መርከብ አንቺ ነሽ። ማርያም ከጊዜ በፊት በአምላክ ልቡና ታስባ ትኖር የነበረች ናት። ማርያም የእግዚአብሔር የመቅደሱ አዳራሽ ናት። (#በግእዝ፦ ሐመረ ተርሴስ ዘሰሎሞን አንቲ እንተ አዕተዉ ጠቢባን ወርቀ ያፌዝ ባቲ። ማርያም ህሉት ውስተ ልበ አምላክ እምቅድመ ጊዜ። ማርያም ታዕካ ለእግዚአብሔር ጽርሐ መቅደሱ)።

## 💖መልክአ ገብርኤል ካልእ💖

**ገብርኤል፦** ከምስጋና ዝም ለማይሉ ከንፈሮችህ ሰላም እላለሁ። ከሊቃናት አንዱ የምትሆን የአርያም ካህን ገብርኤል ሆይ ልመናዬን ከደመናት በላይ አሻግር። (#በግእዝ፦ ሰላም ለከናፍሪከ እለ ኢያረግማ እምቅዳሴ። ካህነ አርያም ገብርኤል እምነ ሊቃናት አሐዱ ቃለ ስእለትየ ደመናተ አዕዱ)።

## 💗መልክአ ዑራኤል💗

የይቅርታና የምሕረት መልአክ የከበርክ ዑራኤል ሆይ ስለእኛ ወደ እግዚአብሔር ለምን። ዑራኤል መዓዛው ሕይወት የሆነ ናርዶስ ነው። ከፍ ያለ የሰማይ መልአክ የከበረ ዑራኤል ሆይ በስቅለት ጊዜ የእውነት በኵር ደምን ስትረጭ ሽመላ የተአምርህ ቃል በምድራችን ታየ። (#በግእዝ፦ ዑራኤል ክቡር መልአከ ምሕረት ወሣህል ተንበል በእንቲኣነ ኀበ እግዚአብሔር ልዑል። ዑራኤል ናርዶስ ዘመዓዛሁ ሕይወት። ዑራኤል ክቡር መልአከ ሰማይ ምጡቅ አስተርአየ ውስተ ምድርነ ቃለ ተአምሪከ ማዕነቅ በጊዜ ስቅለት እንዘ ትነዝኀ ደመ በኵር ዘጽድቅ)።

## 💗መልክአ ጊዮርጊስ💗

ጊዮርጊስ ሆይ ክፉ የሆነ የቢሩት ደራጎንን ያሸነፍክ ነህ። ባለ መድኀኒት ጊዮርጊስ ከበሽታ የሚያድን ነው። (#በግእዝ፦ ጊዮርጊስ መዋዒ ደራጎነ ቢሩት ፀዋግ። ዐቃቤ ሥራይ ጊዮርጊስ መፈውሰ ደዌ)።

## ❤መልክአ ክርስቶስ ሠምራ❤

የተክለ ሃይማኖትን መንገድ ተከትለሽ ጣናን መኖሪያ አደረግሻት። (#በግእዝ፦ እንዘ ትተልዊ ዘተክለ ሃይማኖት ፍና እፎኑሙ ረሰይኪያ በዓተ ለፃና)።

## 💗መልክአ ተክለ ሃይማኖት💗

የፊደሉ መጀመሪያ መስቀል ለሆነ የከበረ ስምና ከፍ ያለ የስምህ መታሰቢያ ሰላምታ ይገባል። ምስጋናን እንጂ ከንቱ ነገርን ላልተናገሩ ከንፈሮችህ ሰላም እላለሁ። ተክለ ሃይማኖት ሆይ

ጨለማን የምታስወግድ ፀሐይ ነህ:: (#በግእዝ፦ ሰላም ለዝክረ ስምከ ዘጥንተ ፊደሉ መስቀል ስም ክቡር ወስም ልዑል:: ሰላም ለከናፍሪከ ዘኢነበባ ከንቶ እንበለ ዳእሙ አእኰቶ:: ተክለ ሃይማኖት ፀሐይ ለጽልመት ዘተአትቶ)::

### ❤መልክአ መርቆሬዎስ❤

ሰማዕት መርቆሬዎስ በጥቁር ፈረስ ላይ የሚጫን [የሚቀመጥ] ነው:: ሰማዕት መርቆሬዎስ በሃይማኖትና በፍቅር ያጌጠ ነው:: (#በግእዝ፦ መርቆሬዎስ ሰማዕት መስተፅዕነ ፈረስ ጸሊም:: መርቆሬዎስ ሰማዕት ሥርግወ ሃይማኖት ወፍቅር)::

### ❤ማሕሌተ ጽጌ❤

የኖኅ የኪዳኑ ምልክት ቀስተ ደመና ማርያም ናት:: ማርያም ዕፀ ሳቤቅና ያማረ ኮከብን የወለደች የያዕቆብ ምሥራቅ ናት:: የብርሃን ዕለት የሰንበታት ሰንበት ማርያም ሆይ መጽሐፍ እንዳለ በፈጣሪና በፍጡራን መካከል የዕረፍት የኪዳን ምልክት የሆንሽ ነሽ:: ምሥጢርን ያዩ ነቢያት የተዘጋሽ የአበባ የአትክልት ቦታና የተዘጋሽ የምሥራቅ ደጅ አሉሽ:: የትንቢት አዝመራ ማርያም እንግዳ የሆነ የአበባ ዘመን ናት:: ማርያም ሆይ እናትሽ አበባን የወለደች ሦስተኛዋን ቀን [ማክሰኞን] እና የምታበራ ፀሐይን ያስገኘች አራተኛ ቀን [ረቡዕን] ትመስላለች:: ዳግመኛም በሰማይና በምድር ላሉ ዕረፍት የሆንሽ ሰባተኛዋን ቀን [ቅዳሜን] ትመስላለች:: እግዚአብሔር አንችን ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶም በሆንነ እንደ ገሞራም በመሰልነ ነበር:: ማርያም ሆይ መድኀንን የአበብሽ የምልክት በትር ነሽ:: ከጨረቃ ይልቅ ውብ የሆነ የሚያበራ ሕፃንን አቅፈሽ ሳለ ዐይኗን ወደ ሰማይ ከፍ አድርጋ ሳቤላ ተአምርሽን ተመለከተች:: ማርያም ሆይ ያለአንቺ ወደ ላይ የሚወጣ ጸሎትና ልመና የለም:: ማርያም ሆይ የታዴዎስ የስንዴ እሸቱ እና ፍሬን ያበብሽ የበርተሎሜዎስ ወይን ነሽ:: ማርያም ሆይ የጴጥሮስ ጥላው የጳውሎስ ጥምጥሙ ነሽ:: በአንቺ ሙታን ሕያዋን ሆኑ:: የጊዮርጊስ የመንግሥቱ ዘውድና የአበባ አክሊል ማርያም ሆይ ከሚያበራ ባሕርይ ከሚባል ዕንቍ ይልቅ የጠራ የወርቅ ቦርቦርቴ ዙሪያ አንቺ ነሽ:: አንቺ ሁሉን ታሰግጂለታለሽ ለአንቺም እርሱ ይሰግዳል:: ከአበቦች ውበት ይልቅ የምታበሪ የእስጢፋኖስ ጽጌረዳ አንቺ ነሽ:: በምስክርነት አደባባይ በአበባሽ መዓዛ የሰከረ ሰው በድንጋይ መወገር ገለባ ይመስለዋል እሳትም ቀዝቃዛ የባሕር ውሃ ይመስለዋል:: ማርያም ሆይ ከኬፋ የገዛሁሽ ሃይማኖቴ ነሽ:: ሃይማኖቱን የካደ አንድ ሰው በአሳተው ሰይጣን ፊት አንቺን መካድን እንቢ ባለ ጊዜ ድንግል ሆይ አንቺን ማመኑ ነፍሱን ለማዳን ጠቀመችው:: ማርያም ሆይ ኀዘንን የምታስረሺ ደስታ ነሽ:: በእሾሆች አይሁድ መካከል አበባን ያበብሽ የበጋ ያይደለ የቆላ የሱፍ አበባ ነሽ:: ማርያም ሆይ ርኅራኄሽ መልአክን ሕፃንን ከመቅሰፍ አስትቶታል:: (#በግእዝ፦ ቀስተ ደመና ማርያም ትእምርተ ኪዳኑ ለኖኅ:: ማርያም ዕፀ ሳቤቅ ወምሥራቅ ዘያዕቆብ ወላዲቱ ለሥርግው ኮከብ:: በከመ ይቤ መጽሐፍ ማዕከለ ፈጣሪ ወፍጡራን ለዕረፍት ዘኮንኪ ትእምርተ ኪዳን:: ሰንበተ ሰንበታት ማርያም ዕለተ ብርሃን:: ሰመዩኪ ነቢያት እለ ርእዩ ኅቡዓተ ገነተ ጽጌ ዕፁተ ወኖኅተ ምሥራቅ ኅትምተ:: ማዕረረ ትንቢት ማርያም ዘመነ ጽጌ እንግዳ:: ትመስል

እምኪ ማርያም ዕለተ ኃልስተ ወራብዕተ ዘወለደት ጽጌ ወፀሐየ ዓለም ብርሀተ:: ወካዕበ ትመስል ሳብዕተ ዕለተ:: ለእለ በሰማይ ወምድር ዘኮንኪ ዕረፍተ:: ከመ ሰዶም እምኮነ ወከመ ገሞራ እመሰልነ እግዚአብሔር ኢያኪ እመ ኢያትረፈ ለነ በትረ ተአምር ማርያም እንተ ጸገይኪ መድኅነ:: እንዘ ተሐቅፊ ሕፃነ ዘይጸድል እምሥነ ዕብላ መንገለ ሰማይ አዕይንቲሃ አልዒላ ተአምረኪ ነጸረት ሳቤላ:: አልቦ ጸሎት ወአልቦ ትንባሌ እንበሌኪ ማርያም ዘየዐርግ ሉዓሌ:: ሠዊተ ሥርናዩ ለታዴዎስ ወለበርተሎሜዎስ ወይኑ እንተ ጸገይኪ አስካለ:: ማርያም ለጴጥሮስ ጽላሎቱ ወለጳውሎስ ሰበኑ ብኪ ምውታን ሕያዋነ ኮኑ:: ክበበ ጌራ ወርቅ ጽሩይ እምዕንቈ ባሕርይ ዘየሐቱ:: አክሊለ ጽጌ ማርያም ለጊዮርጊስ ቀጸላ መንግሥቱ:: አንቲ ኵሎ ታሰግዲ ሎቱ ወለኪኒ ይሰግድ ውእቱ:: ጽጌረዳሁ ለእስጢፋኖስ እምሥነ ጽጌያት ዘትጸድሊ:: በመዓዛ ጽጌኪሰ ለዘበዐውደ ስምዕ ሰክረ ውግረተ አዕባን ይመስሎ ኀሠረ እሳትኒ ማየ ባሕር ቈሪረ:: ሃይማኖትየ ማርያም ዘአጥረይኩኪ እምኬፋ:: አሐዱ ነዳይ ዘክሕደ ሃይማኖቶ ኪያኪ ክሂደ ሶበ ዐበየ በቅድመ ሰይጣን ዘአስሐቶ አሚነ ዚኣኪ ድንግል ለአድኅኖ ነፍሱ በቍዐቶ:: ማርያም ፍሥሓ ዘታረስዒ ኀዘነ:: ጽጌ ደንጎላ ዘቈላ ወአኮ ዘደደክ ዘጸገይኪ ጽጌ በማዕከለ አይሁድ አሥዋክ:: ርኅራኄኪ ማርያም ቀሲፈ ሕፃን አኅደጎ ለመልአክ)::

## ❢መልክአ መድኀኔዓለም❢

**ነገረ ክርስቶስ፦** በሞትህ ሞትን ትገድል ዘንድ ከርቤና ሐሞትን ስለእኔ የጠጣህ ነህ:: በቀራንዮ የተሰቀልክ የዓለም መድኀኒት ክርስቶስ ሆይ ስለድንግል ማርያም ብለህ ማርኩህ በለኝ:: ያለ አንተ ቃል ቸር የለምና:: መድኀኔዓለም ሆይ ለሰውነቴ ማረፊያ ስጠኝ:: ከዓለም በፊት የነበርክ የዓለም መድኀኒት ክርስቶስ ሆይ የታሰሩ ባሮችህን ታስረህ ፈታሃቸው:: በሞትህም ሙታንን አስነሣህ:: (#በግእዝ፦ ዘሰተይከ በእንቲኣየ ከርቤ ወሐሞተ በሞተ ዚኣከ ከመ ትቅትል ሞተ:: መድኀኔዓለም ክርስቶስ በቀራንዮ ስቁል በለኒ መሐርኩከ በእንተ ማርያም ድንግል እስመ ኄር አልቦ እንበሌከ ቃል:: መድኀኔዓለም ሀበኒ ለሰብእናየ ምዕራፈ:: መድኀኔዓለም ክርስቶስ ዘእምቅድመ ዓለም ነበርከ:: አግብርቲከ ዘተሞቅሑ ተሞቂሐከ ፈታሕከ ወበሞትከ ሙታነ አንሣእከ)::

## ❤መልክአ ሕማማት❤

**ነገረ ማርያም ወክርስቶስ፦** መና ክርስቶስን የወለድሽ ቋና ማርያም ሆይ ሰላም ለአንቺ ይሁን:: በሚመላለስ ጊዜ ድምፅ ታሰሚ ዘንድ በአንቺ የወርቅ ሻኩራ ያለብሽ የካህናት አለቃ የአሮን ልብሱ ማርያም ነሽ:: በማሕፀኗ ብሩህ ከሆነ ከፀሐይ ጸዳል የተነሣ ብርጋና የሚባል ወፍን የምትወልጂ ስትታዩ የምታበሪ ዕንቍ ማርያም ሆይ ሰላም ለአንቺ ይሁን:: የሌሊት ጨለማን ያስወገድክልን የሕይወት ብርሃን ኢየሱስ ነህ:: እህል ማርያም ሆይ ሰላም ለአንቺ ይሁን:: የአብርሃም ድንኳን ሆይ ሰላም ለአንቺ ይሁን:: (#በግእዝ፦ ሰላም ለኪ ማርያም ጎሞር ወላዲተ ክርስቶስ መና:: ለሊቀ ካህናት አሮን ማርያም ልብሱ ወጸናጽለ ወርቅ ብኪ ዘስክዕተ በናዕሱ ከመ ትድምፂ ጊዜ ያንሶሱ:: ሰላም ለኪ ማርያም ባሕርይ ጽድልተ ንጻሬ ወዜና እምፀዳለ ፀሐይ ብሩህ

በማሕፀና ዘትወልድ ያፈ ብርጋና። ዘአግሐስከ ለነ ጽልመተ ሌሊት ኢየሱስ ብርሃነ ሕይወት። ሰላም ለኪ ማርያም እክል። ሐይመተ አብርሃም አብ ሰላም ለኪ)።

## ▶መልክአ ኢየሱስ◀

ጌታ ሆይ ኢያሱ በራሱ ላይ የስምህን ዘውድ በተቀዳጀ ጊዜ የጠላት ሀገሮችን ወረሰ። ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአትን ሁሉ የሚያስተሠርይ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ከመቀየም ይልቅ የውሃትን የሚወድ ነው። አቤቱ የአፍ መዝጊያ የሆነች ዝምታን ስጠኝ። ኢየሱስ ክርስቶስ የእውነትና የሃይማኖት ጣሪያ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የሱሳ ነቢይ የሆነ የዳንኤል ሞገስ ነው። ጨለማን ያስወገድክ ብርሃን ክርስቶስ ነህ። (#በግእዝ፦ አክሊለ ስምከ እንዘ ይትቄጸል በርእሱ አህጉረ ፀር ወረሰ ኢያሱ። ኢየሱስ ክርስቶስ መስተሥርየ ኵሉ ጌጋይ። ኢየሱስ ክርስቶስ መፍቀሬ የውሃት እምተቀይሞ ጸግወኒ ማዕፆ አፍ እንተ ይእቲ አርምሞ። ኢየሱስ ክርስቶስ ጠፈረ ሃይማኖት ወጽድቅ። ኢየሱስ ክርስቶስ ሞገሰ ዳንኤል ነቢየ ሱሳ። ክርስቶስ ብርሃን ዘአሰሰልከ ጽልመተ)።

## ➡መልክአ ፋሲለደስ⬅

ክብ የሆኑ የዐይን ብሌኖች ከንቱ ነገርን እንዳያዩ መጠበቅን ለተጠበቁ ቅንድቦችህ ሰላምታ ይገባል። ኀያል ፋሲለደስ ሕግና ሥርዓትን የሚጠብቅ ነው። (#በግእዝ፦ ሰላም ለቀራንብቲከ እለ የዐቅባ ዐቂበ ከመ ኢይርአያ ከንቶ ብንተ አዕይንት ክኡብ። ፋሲለደስ ኀያል ዐቃቤ ሥርዓት ወሕግ)።

## ❀መልክአ እስጢፋኖስ❀

ቂምንና በቀልን እንዳያስብ መንፈስ ቅዱስ ብልህ ላደረገው ኅሊናህ ሰላም እላለሁ። የሮሜ ሰዎች ዐውደ ዓመታቸው የምትባልና የፍቅር ወር በሆነችው በጥር ወር ለሆነ የነፍስህ መውጣት ሰላም እላለሁ። (#በግእዝ፦ ሰላም ለኅሊናከ መንፈስ ቅዱስ ዘአጥበቦ ከመ ኢየኀሊ ቂመ ወበቀለ። ሰላም ለፀአተ ነፍስከ በሠርቀ ወርኀ ጥር ወርኀ ሱላሜ እንተ ይእቲ ትትበሀል ዐውደ ዓመቶሙ ለሰብአ ሮሜ)።

## ❀መልክአ ኤዎስጣቴዎስ❀

አባ ሆይ ባሕርን የከፈልክ ሁለተኛው ሙሴ ነህ። የኢያሪኮ ባሕርን ወጥቶ ተሻገረ፣ መጎናጸፊያውም መርከብን ሆነችው። (#በግእዝ፦ አባ ከፋሌ ባሕር ዳግማይ ሙሴ። ባሕረ ኢያሪኮ ዐደወ ወሠረረ ወአጽፋኒ ኮነቶ ሐመረ)።

## ☦መልክአ ካህናተ ሰማይ☦

ደጋግ የሆኑ ካህናተ ሰማይ ከበቀል የራቁ ናቸው። (#በግእዝ፦ ካህናተ ሰማይ ኄራን ርትቃን እምተበቅሎ)።